# ዴሞክራሲያ

************************************************************

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሣን*

************************************************************

ቅፅ 39 ቁ.1 ጥር 2006 ዓ. ም


## ሀገር! ትግልና የትግል አጋር

ባለፈው ግማሽ ምዕተ-ዓመት በኢትዮጵያ ውስጥ በተካሄደው የፖለቲካ ትግል የኢትዮጵያን መሠረታዊ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ሁኔታዎችን ለመለወጥ ከፍተኛ መስዋዕትነት የተከፈለ ቢሆንም ጥቂት ጥገናዊ ለውጥ ከማምጣትና በአፄው ዘመን የነበረው ጉልተኛ ሥርዓት ፈጥሮት የነበረውን የጭሰኛና የባላባት ግንኙነት ከማፍረስ ባሻገር እስከ አሁን ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት በማድረግና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ማዋለድ አልቻለም። እንዲያውም ከአፄው ሥርዓት በኋላ የመጡት ተከታታይ አምባገነን አገዛዞች የጉልተኛውን ሥርዓት በመንግሥት የመሬት ባለቤትነት በመተካት አርሶ አደሩ የመሬቱ ባለቤት እንዳይሆን አድርገውታል። አሁንም ሕዝባችን በጨቋኝና አምባገነን አገዛዝ ሥር እየማቀቀ ነው፤ አሁንም ሕዝባችን ሰላም አላገኘም፤ አሁንም ጥቂት የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ያለቅጥ ሲበለጽጉ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በድህነት አረንቋ ውስጥ ይገኛል፤ አሁንም ስደቱ አላበቃም። ከሁሉም የከፋው ደግሞ የዘርና የአድልዎ ፖለቲካ ሀገራችንን እየናጣትና ለባሰ መከፋፈልና መናቆር አደጋ ማጋለጡ ነው። በአጠቃላይ አሁንም ሕዝባችን ከጨለማው ዘመን አልወጣም።

በአሁኑ ሰዓት በመላ ሀገሪቷ ውስጥ ከቀን ወደ ቀን በአደገኛ ሁኔታ እየተበራከተና እየተስፋፋ የመጣው የዜጎች መፈናቀል፣ ሥራ-አጥነት፤ ዓይን ያወጣ ዘረፋና ሙስና ችግሩን እያገዘፈው ይገኛል። ይህ ሁኔታ በተለይም ወጣቱ ትውልድ በሀገሩ ላይ ተስፋ እንዲቆርጥ በማድረጉ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በየቀኑ ሀገር ጥለው እንዲሰደዱ አድርጓል። የተለያዩ የአፍሪካና የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች በኢትዮጵያውያን ስደተኞች ተጥለቅልቀዋል። በነዚህ ሀገሮች እሥርቤቶች ውስጥ የሚማቅቁ ኢትዮጵያውያንን ቁጥር ለመገመት ከሚያስቸግር ደረጃ ተደርሷል። በባዕዳ ን ሀገሮች በሚኖሩ ዜጎቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ግፍና ሰቆቃ የሰው ልጅ ከሚገምተው በላይ ሆኗል። በሳውዲ ዓረቢያና በሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች በዜጎቻችን ላይ የሚደረገው ድብደባ፤ ግድያ፤ ሴቶችን አስገድዶ መድፈርና ንብረት ቀምቶ በአሰቃቂ ሁኔታ ከሀገር ማባረር ችግሩ የደረስንበትን አስከፊና አሳፋሪ ሁኔታ በግልጽ አመላካች ነው። ይህ ከፍተኛ ብሄራዊ ውርደት ሀገራችን ላይ እንዲደርስ ያደረገው የህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ እንደሆነ ለማንም ግልፅ ነው። አሁን ሀገራችን የምትገኝበትን ሁኔታ ስንመረምረው የፓለቲካ፤ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ በመሄዱ የሀገረቷን

ህልውና መፈታተን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ነው የምንገነዘበው። የትግሉም ሁኔታ ዘርፈ ብዙ እየሆነና እየተወሳሰበ በመሄዱ የኃይል አሰላለፉንም እንደዚሁ እየተለዋወጠ እንዲሄድ አድርጓል። በተለይ ባለፉት ሃያ ሦስት ዓመታት የተደረገው የፖለቲካ ትግል ከቀደሙት አሥርተ-ዓመታት የዴሞክራሲና የፍትህ ትግል ለየት ያለ ሆኖ እናገኘዋለን።

ህወሓት/ኢህአዴግ ኤርትራ እንድትገነጠል እውቅና ከመስጠት አልፎ በሕገ-መንግሥቱ ተብዬው ውስጥ አንቀጽ ሠላሳ ዘጠኝን በመሰንቀርና መገንጠልን ሕገ-መንግሥታዊ መብት በማድረግ ሀገሪቱን ለቀጣይ አደጋ እንድትጋለጥ አድርጓታል። በመሆኑም አሁን የምናደርገው ትግል ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሥረታ ብቻ ሳይሆን ሀገሪቱን ከመፈራረስ ለማዳንም ሆኗል። በሀገሪቱ ላይ የተጋረጠው የመከፋፈል ስጋት እውን እንዲሆን አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የገዢ ቡድን የተጫወተውና እየተጫወተ ያለው ሚና ትልቁን ድርሻ የሚይዝ ሲሆን፣ የመገንጠል ጥያቄን የሚያቀነቅኑ ጠባብ ብሄርተኛና አክራሪ ቡድኖችና የውጭ ደጋፊዎቻቸውም ሊፈጥሩ የሚችሉት አደጋ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ስለዚህ የሀገራችን ዘላቂ ብሄራዊ ጥቅም ምንድን ነው? ብሄራዊ ጥቅምን ለመጠበቅ ትግሉን በምን መልክ ማካሄድ ይኖርብናልን? አደጋውስ ምንድን ነው? ትግሉ የትና መቼስ ነው መደረግ ያለበት? ለዚህ ትግል አጋር ሊሆኑ የሚችሉትስ እነማን ናቸው? የሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚሹ ናቸው።

የሀገራችን ዘላቂ ጥቅም የሚጀምረው በአንድነቷ ላይ ነው። አንድነቷ ከሌለ ሀገራችን የለችም። ሀገር ስትኖረን ነው ጭቆናን አስወግደን በምትኩ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መመሥረት የምንችለው። ስለዚህም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የሚያደርጉት ትግል ዴሞክራሲያዊት የሆነች አንድነቷ የተረጋገጠ ኢትዮጵያን መመሥረትን ጣምራ ግቡ ያደረገ መሆን አለበት። የኃይል አሰላለፉንም ስናይ እነዚህን ግቦች ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት። ለዚህ ጣምራ ግብ መሳካት በሚደረገው ትግል ዋናው ኃይል የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሆነና በተግባርም ታጋይ ድርጅቶች ይህን የትግሉ ባለቤት የሆነውን ሕዝብ በማደራጀትና ተባብረውም በመሥራት የማይበገር ሕዝባዊ ኃይል ሊፈጥሩ ሲችሉ እንደሆነ ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በፅኑ ያምናል። ለዚህም ነው ድርጅታችን የተቃዋሚ ድርጅቶች ተባብረው ጠንካራ ኅብረት በመፍጠር ሕዝብን እንዲያስተባብሩ ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርግ የቆየው።

በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳን ዋናው የትግሉ ባለቤት ሕዝቡ እንደሆነ የታወቀ ቢሆንም ሁለቱን ሕዝባዊ ዓላማዎች ማለትም የሀገሪቱን አንድነት መጠበቅንና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መፍጠር፤ ሊደግፉ የሚችሉ ሌሎች የውጭ ኃይሎችን ማሰባሰብና እርዳታን ማግኘት ትግሉን በአፋጣን ለማካሄድና ከግባችን ለመድረስ እንደሚረዳ እሙን ነው። ከዚህም አንፃር ነው ሌሎች ኃይሎችን በተለይም እራሱን ከኢትዮጵያ ውጭ አድርጎ የሚያየውን ሻዕቢያን በትግላችን ላይ የሚኖረውን አሉታዊም ይሁን አወንታዊ ተጽዕኖ የምናየውና የምንመረምረው። እነዚህ ኃይሎች የዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ናቸው? እነዚህ ኃይሎች የኢትዮጵያን አንድነት የሚፈልጉ ኃይሎች ናቸው? በየትኛው የትግል ዘርፋችን ሊያግዙን ይችላሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች በጥሞና መመርመር ያስፈልጋል።

የመለሰ ዜናዊ ህወሓት 21 ዓመት ሙሉ ኢትዮጵያዊነትን ሲገዘግዝ ቢኖርም በኢትዮጵያ ሕዝብ ሆደ-ሰፊነትና ጠንካራ ኢትዮጵያዊነት ሀገራችን ህወሓት በፈለገው መልክ ሳትናድ ቆይታለች። ይህ ሀገርን ከብሔርና ከክልል ጋር አቆራኝቶ የማፋጀት ስትራቴጂ የትምህርት ቀመሱ ብሄረተኛ አጀንዳ ብቻ በመሆኑ ሀገራችን አሁንም ጠንክራ ለመቆም ችላለች። ሻዕቢያ በህወሓት ተባባሪነት ኤርትራን ሲገነጥል ነፃ የሕዝብ ውሳኔ እንዲካሄድ ያልፈቀደበት ምክንያት፤ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ተወላጅ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ስለ ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሚያቀርቡትን አማራጭ በመፍራትና አፋርና ሌሎች በኤርትራ ውስጥ ያሉ ብሄረሰቦች ኢትዮጵያዊነትን በማውለቅ መገንጠልን ይመርጣሉ ተብሎ ጥርጣሬ እንኳን ባለመኖሩም ጭምር ነው።

ስለዚህ ኤርትራ ተገነጠለች የተባለው "ውሳኔ-ሕዝብ" ተካሄደ በተባለበት በራሷ በኤርትራ ውስጥ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ በሌለበት፣ የተለያዩ አማራጮች በነፃነት ለሕዝብ ባልቀረቡበት፣ መረጋጋት በሌለበትና ከመገንጠል በመለስ አማራጭህ "ባርነት" ነው በሚል የሻዕቢያ መርዝ በተሞላ ፖለቲካዊ ድባብ ውስጥ ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምና ሉዓላዊነት የገፈፈና ሕዝብን በምንም መልክ ሊወክል በማይችል፣ በፍትሃዊ የሕዝብ ምርጫ ሕዝባዊ ውክልናን ያላገኘ ነፍጠኛ ቡድን ኢትዮጵያን በሚገዛበትና የቡድኑን ወሳኔ በሕዝብ ላይ በኃይል በሚጭንበት ሁኔታ ነው። ስለዚህም ነው የሻዕቢያን "መንግሥትነት"ና የኤርትራን "ነፃ" ሀገርነት የማንቀበለው። ከአንዳንዶች እንደሚደመጠው "የተባበሩት መንግሥታት ኤርትራን እንደ ሀገር አውቋታል፤ ምንም ማድረግ አይቻልም"፣ "የተቀረውን የኢትዮጵያ ክፍል ማዳን ነው የሚሻለው" የሚለው አባባል ደግሞ ጨርሶ አያስኬድም። የአንድን ሀገር ህልውና ከጊዜያዊ አቅም ማጣት ጋር ማያያዝና ጥሎት የሚያልፈውንም ጠባሳ በትክክል አለመገንዘብ ከባድ ስህተት ከመሆንም አልፎ በታሪክ ያስጠይቃል። ለምሳሌ በታሪክ አጋጣሚ ጣሊያን ለ60 ዓመታት ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመነጠል የቻለች ቢሆንም ለሀገራዊ አንድነት ሲደረግ የነበረውን ተጋድሎ ግን ሊገታው አልቻለም። በዚህ ተጋድሎም ኤርትራ ውስጥ የተወለዱ በርካታ ኢትዮጵያውያን የከፈሉትን መስዋዕት ታሪክ ሁሌም የሚዘክረው ነው። አሁን ደግሞ ሻዕቢያ ለ23 ዓመታት መነጠል በመቻሉ የኤርትራ ጉዳይ ያለቀለት ጉዳይ ነው ብሎ የሚያስብ ካለ የኢትዮጵያን ሕዝብና ታሪክ በትክክል ያልተገነዘበ ብቻ ነው። የኤርትራና የተቀረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ግንኙነት የሀገሪቷን ዜጎች ግልጽ ፍላጎትና ዘላቂ ጥቅም በትክክል ባገናዘበ መልኩ ፍትሃዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ እስካልተፈታ ድረስ አሁን ባለው ሁኔታ በሀገራችንም ሆነ በምሥራቅ አፍሪቃ ቀጠና ሰላምና መረጋጋት ይኖራል ማለት ዘበት ነው። ሻዕቢያም ቢሆን የራሱ ህልውና የሚጠበቀው በተዳከመችና በተከፋፈለች ኢትዮጵያ መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል። ይህንንም ለማሳካት ተግቶ እየሠራ ከመሆኑም በላይ ምን ጊዜም ቢሆን ቦዝኖም እንደማያውቅ የታወቀ ነው። በዘመን አመጣሹ የፓለቲካ ግርግር ኢሳያስ ተራማጅ ነው፤ ሻዕቢያ ኢትዮጵያን ይወዳ ል እየተባለ ሻዕቢያን ለመቀባባት የሚደረገው ሩጫ ወገንን ከጠላት የቀላቀለ አደገኛ አካሄድ ነው።

ያለፉትን የትግል ዓመታት ስንመረምር በሀገሪቱ ውስጥ እንቅስቃሴ ያደረጉት የፖለቲካ ድርጅቶች ከተነሱበት ዓላማና ግብ አንፃር ድርጅቶቹን በሁለት ጎራዎች ከፍሎ ማየት ይቻላል። በአንድ በኩል ኢትዮጵያን እንደ ሀገራቸው አድርገው የሚያዩና በሀገሪቱ ውስጥ

የነበረውን የአስተዳደር በደልና የመብት ረገጣ ለመለወጥ የየራሳቸውን መፍትሄ በማቅረብ የታገሉ ሲሆን በሌላው ጎራ ደግሞ ኢትዮጵያን እንደ ሀገራቸው የማያዩ፣ ሕዝቧን እንደ ባዕድ የሚያዩ አንዳንዶች ደግሞ ጨርሶ እንደጠላት የሚቆጥሩና፣ እንደ መፍትሄም መገንጠልን እንደ ብቸኛ አማራጭ የሚያቀርቡ ናቸው። ጠባብ ብሄርተኛ የሆኑት የፖለቲካ ኃይሎች፣ በተለይም ህወሓት፣ ዋነኛውና የመጀመሪያው የሀገሪቱ ችግር "የብሄር ችግር" ነው በሚል አስተሳሰብ ሀገሪቱን ሕዝቡ በሚናገረው ቋንቋ መሸንሸን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ኤርትራን በቅኝ ግዛትነት እየገዛች ኖራለች የሚለውን የሻዕቢያን ፕሮፖጋንዳ በመቀበል የሀገሪቱ ሉዓላዊነት እንዲገሰስና የሰሜኑ ሕዝብም እንዲነጠል አድርጓል።

ሌላው መጠቀስ ያለበት ጉዳይ በአካባቢው ያሉ የውጭ መንግሥታት ብሄራዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ትንቅንቅ በሀገራችን የውስጥ ፓለቲካ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ጣልቃ መግባትና ተፅእኖ ማድረግ መቻላቸው ነው። የራሳችንን ነፃ መንግሥት እናቋቁማለን የሚሉ ብሄረተኛ ኃይሎችን ወታደራዊ የበላይነት እንዲኖራቸው ያደረገው የነዚሁ የውጭ መንግሥታት ድጋፍ ነው። ሻዕቢያና ህወሓት የመንግሥት ሥልጣን እንዲቆጣጠሩና ሀገሪቷንና ሕዝቧን ባፈተታቸው መልክ እንዲያሽከረክሯት ካደረጉት አገሮች ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት ግብፅ፤ ሱዳን፣ ኢራቅ፣ ሶሪያና ሱማሊያ…ወዘተ የሰጡት ድጋፍ መሆኑ እራሳቸውም አይክዱትም። ግብፅና ሱዳን በዓባይ ወንዝ ምክንያት፣ ኢራቅና ሶሪያ ዓረባዊት ዓለም ለሚሉት የቅዠት ፖለቲካ እንዲሁም ሶማሊያ በኦጋዴን ምክንያት የፈጠሩት ተፅእኖ አሁን ሀገራችን ላለችበት የፖለቲካ ምስቅልቅልና ብሄራዊ አደጋ ቀላል የማይባል አስተዋጽዖ አድርገዋል። የግብፅ መንግሥት በተለይም ከ1960ዎቹ ጀምሮ በሶማልያና በኤርትራ ሰፊ ዘመቻ በመክፈት የኃይል አሰላለፉን በመቀየር ከፍተኛ ተፅእኖ መፍጠር ችሏል። ሶማልያም ነፃነቷን ከተጎናጸፈችበት ቀን ጀምሮ የኦጋዴንን የይገባኛል ጥያቄ እንድትገፋበትና ጦርነት እንድትጀምር፣ የግብፅ መንግሥት ገፋፍቷታል። የዓረብ አገሮችም በደጋፊነት እንዲሰለፉ ከማድረግ አልፎም በጦርነቱም ውስጥ በቀጥታ ተሳትፈዋል። እንዲሁም ኤርትራም ተገንጥላ የራሷን መንግሥት እንዲትመሠረት በሚል የመጀመሪያዎቹን የጀብሀ ተጋዳዮችን አሌክሳንደሪያ ላይ በማሰልጠንና ወደ ኤርትራ በመስደድ ጦርነቱን ኢትዮጵያ ላይ ለኩሰዋል። ይህን ኢትዮጵያን የማዳከሙንና የመበታተኑን ሥራ የሱዳን፤ የሶማሊያና የግብፅ መንግሥታት በመተባበርና በግልጽ የተንቀሳቀሱበት ጉዳይ ነው። በተለይም የሶማሌው የዚያድባሬ መንግሥት የረዥም ጊዜ ዕቅድ ኦጋዴንን ወደ ሱማልያ ለመጠቅለል በመሆኑ፣ የምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጭ ግንባር በሚል ስያሜ ሀርጌሳና ሞቃዲሾ የተሰባሰቡ የሶማሊያ ዜጎችን አደራጅቶ ኢትዮጵያን ከመውረር አልፎ የኤርትራ፤ ትግራይ፤ የኦሮሞ፤ የአፋር፤ የሲዳማ፤ የአደሬ ነፃ አውጭ ድርጅቶችን በመርዳት፣ ግማሾቹም እራሱ በማቋቋም፣ ኢትዮጵያን ሲያተራምስ መቆየቱ በግልጽ የሚታወቅ ሃቅ ነው።

የኤርትራው ህግሓኤ (ሻዕቢያ) የመጨረሻ ግቡን ለማሳካት ከሶማሌው መንግሥት ባልተናነሰ መልክ በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠሩትን ብሄረተኛ ድርጅቶች እየተጠቀመ የኢትዮጵያን ህልውና እንደተፈታተነና አንዳንዶቹንም ሻዕቢያ ራሱ እንዳቋቋማቸው ይታወቃል። ሻዕቢያ ከሶማሌ መንግሥት ባልተናነሰ የግብፅና የሱዳን አጀንዳ አስፈጻሚ እንደሆነ በግልጽ የሚታይ ሃቅ ነው። ታዲያ አሁን ኢሳያስ ለኢትዮጵያ ዴሞራሲያዊ

ተቆርቋሪና ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚዎች ህወሓት/ኢህአዴግን እንዲያቸንፉ ደፋ ቀና የሚል ሰው ነው እየተባለ ሲነገርለት እጅግ የሚያስገርም ብቻ ሳይሆን የሚያሳፍርም ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ የሚጀምረው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ነው የሚል አምባገነን እንዴት የኢትዮጵያ ወዳጅ ሊሆን ይችላል? ከውልደቱ ጀምሮ እስካሁኗ ሰዓት ድረስ በኢትዮጵያ ታሪክና ሉዓላዊነት ላይ አነጣጥሮ የሚጓዘው ኢሳያስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጅ አይደለም፤ ሆኖም አያውቅም ሊሆንም አይችልም። ወዳጅ ሊሆን ይችላል ብለን ካሰብን ከእባብ እንቁላል እርግብ እንደመጠበቅ ይሆናል።

ሻዕቢያ ኤርትራን ተቆጣጥሮ "መንግሥት" ነኝ ካለበት ጊዜ ጀምሮ በቀይ ባህር ዳርቻና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ወታደራዊ የበላይነት የመያዝ ህልም ስለነበረው ከአቅም በላይ የሆነ ሰፊ ወታደራዊ ተቋም ለመግንባት ጥረት ማድረጉ የአደባባይ ሚስጥር ነው። የዚህም ወታደራዊ የበላይነት ስሌት ደግሞ የአካባቢንና ዓለምአቀፍ ኃያላትን ጥቅምና ፍላጎት አስጠባቂ በመሆን የቅጥረኝነት ሥራ ለመሥራት ከፍተኛ የኤኮኖሚ ጥቅም አገኝበታለሁ ከሚል ስሌት እንደሆነም ግልጽ ነው። ኃያላን መንግሥታት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያላቸውን የፀጥታ ስጋትና ጥቅማቸውን የማስጠበቅ ሥራን ለህወሓት በመስጠታቸው (በሶማልያና በሱዳን ውስጥ በአቢዬና በዳርፉር ግዛት የኢትዮጵያን ጦር ያስተውሏል) ምኞቱ የከሸፈበት ሻዕቢያ በብስጭት በሶማሊያ የውስጥ ፓለቲካ እጁን በማስገባትና የኃያላኑ ጥቅም በመጋፋቱ ግብግብ የፈጠረበት ሁኔታ ነው ያለው። ኃያላኑም በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት የኤኮኖሚ ተአቅቦ እንዲደረግበት እርምጃ እስከ መውሰድ የደረሱበትም ጉዳይ ከዚህ ሥጋት ተነስተው ነው። እንደዚህ ያለ አጣብቂኝ ውስጥ የገባው አምባገነን ቡድንና መሪ መተንፈሻ ለማግኘት ምንም ከማድረግ እንደማይመለስ መገንዘቡ ተገቢ ነው። በአንፃሩ የሻዕቢያና የህወሓት የእርስ በርስ መናቆርና አንዱ በሌላው ላይ የበላይነት ለማግኘት የሚያደርጉት ትንቅንቅ ለጋራ ህልውናቸው አስጊ ሆኖ ካገኙት ያለአንዳች ማቅማማት በአንድ ጀንበር ተስማምተው የፓሊሲ ለውጥ ሊያደርጉ እንደሚችሉ መረዳ ቱ ብልህነት ነው። እንዲሁም አሁን እየረዷቸው ያሉትን ድርጅቶችን ተመልሰው ያለምንም ይሉኝታ ለማጥፋት እንደማያቅማሙ በረጅም ታሪካቸው ያሳዩን ጉዳይ ነው። ስለዚህ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ድርጅት ከ"ኤርትራ መንግሥት" (ሻዕቢያ) ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የሻዕቢያን ስትራቴጂያዊ ግቦች በግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በሀገራችን ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጠንቅና መዘዙን በጥሞና መመርመር አለበት እንላለን። ትብብር መደረግ ያለበት ለሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብትና ለህግ የበላይነት ከሚታገሉ የኤርትራ ኃይሎች ጋር እንጂ የሕዝብን መብት ጨፍልቆና የኢትዮጵያን ሕልውና ለማጥፋት ከታሪካዊ ጠላቶቿ ጋር ወግኖ ሌት ተቀን ደፋ ቀና ከሚል አምባገነን ጋር ሊሆን አይገባውም።

ህወሓት የራሱን ህልውና ለማስቀጠልና የአፈናውን ሥርዓት ለማጠናከር በየጎረቤት አገሮች ሊኖሩ የሚችሉ ቀዳዳዎችን ለመድፈን ይረዱኛል ያላቸውን እንቅስቃሴዎች ሁልጊዜም ያደርጋል። በአንዳንድ ምክንያቶች ከአካባቢው ኃይሎች ጋር ሻክሮ የነበረው ግንኙነትና ትብብር ለማለሳለስ የሚደረጉ ጥረቶች እያደረገ መሆኑ እየተስተዋለ ነው። አሁን በቅርቡ የኢትዮጵያን ሰፊ የምዕራብ ድንበር መሬት ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት ዝግጅቱን

አጠናቋል። እንዲሁም የግብፅን ተቃውሞ ለማስቀም ሲል ከጥቂት ጊዜ በፊት ሕዝብን ሲያደነቁርበት የነበረውን የህዳሴን ግድብ ግብፅና ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር ሆነው የጋራ ባለንብረት የሚሆኑበትን ሃሳብ እስከማቅረብ ደርሷል። ለሳውዲ ዓረቢያም እንደዚሁ በመቶ ሺህ ሄክታሮች የሚቆጠር ሰፋፊ ለም የእርሻ ቦታዎች ለመስጠት ተዘጋጅቷል።

ይህ ቡድን ለአለፉት 23 ዓመታት የሀገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም አሳልፎ በመስጠት በተደጋጋሚ ብሄራዊ ክህደት ሲፈጽም የቆየ ቡድን ነው። ይህንን ብሄራዊ ክህደት ሲፈጽም ካለማወቅ፤ ከችኮላ ወይም በደመነፍስ ከመጓዝ የተሠራ ስህተት አይደለም። ከአጠቃላይ የፓለቲካ ስትራተጂውና ግብ ጋር የተያያዘ አካሄድ ነው። ህወሓት ከአንድ አካባቢ የወጣ አናሳ ቡድን በመሆኑ የሀገሪቱን ፓለቲካና ኤኮኖሚ ለመቆጣጠር የውጭ ኃይሎችን የገንዘብ፤ የወታደራዊና የዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ይሻል። ስለዚህም ነው የሀገሪቷን ብሄራዊ ጥቅሞች መረን በለቀቀና ድፍረት በተሞላበት መልክ ለውጭ ኃይሎች በየጊዜው አሳልፎ የሚሰጠው። ለዚህም ነው የምግብ እጥረት ያለባት የሀገራችንን ሰፋፊ ድንግል መሬቶቿን ለሀገሪቷ ዜጎች ከልክሎና አፈናቅሎ ለመካከለኛው ምሥራቅና ለእስያ ሀገሮች ልማታዊ ድርጅቶች በነፃ በሚባል ደረጃ እስከ 99 ዓመት በሚደርስ ውል ፈርሞ የሰጠው። አሁንም ቢሆን ህወሓት የፓለቲካ አካሄዱና ፍልስፍናውን ምንም አልተወለጠም። አደረጃጀቱም እንደዚሁ ከሃያ ሦስት ዓመታት የሥልጣን ዘመን በኋላም የኢህአዴግን አባል ድርጅቶችን አዋህዶ ህብረ-ብሄራዊ ድርጅት ማድረግም አይፈልግም። አሁንም በብሄረሰብ ማንነት ዙሪያ ተደራጅቶና ተከፋፍሎ መፎካከሩን ይጠቀመኛል ብሎ እስካሁንም ድረስ ቀጥሎበታል።

ሌላው አስገራሚ ትእይንት ደግሞ ከ70 ሺህ የኢትዮጵያን ወጣቶችን አስፈጅቶ የተያዘች ባድሚን ለሻዕቢያ ለማስረከብ በሚስጥር ለመደራደር በሱዳኑ በሽር አማካኝነት የሚያደርገው ጥረት ነው። ሰላምና ዕርቅን ማንም የሚጠላ ባይኖርም ከሻዕቢያ ጋር ድርድር ሲባል ግን ሁላችንንም የሚያሳስበን አሁንም በድጋሚ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የሚጎዳና የህወሓትን ደህንነትና ጥቅም የሚጠብቅ በመሆኑ ነው። የሻዕቢያና ህወሓትን ግንኙነት በተመለከተ፣ ህወሓት ገና ከመሠረቱ የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ብሎ የተቀበለና ከሻዕቢያ ጎን በመቆም ከሻዕቢያ ባልተናነስ ትግል ማካሄዱን እንደ አኩሪ ታሪክ ደጋግሞ እንደነገረን አይዘነጋም። ይህን በማድረግ በቁጥጥሩ ሥር ያዋለውን ሕዝብ በከፍተኛ ደረጃ በስህተት ጎዳና እንዲጓዝ ያደረገ ሲሆን የኢትዮጵያ ታሪክ መሠረት የሆነውን የትግራይ ሕዝብ ታሪክ ሳይቀር እንዲበረዝና ቦታ የሌለው እንዲሆን አድርጎታል። ከዚህ ስህተት አመለካከት በመነሳትም ኢትዮጵያችን ታሪካዊ አካሏ የሆነችውን ኤርትራን እንድታጣና ወደብ አልባ እንድትሆን አድርጓል። በዚያን ጊዜ የተሠራውን ታሪካዊ ስህተት የቀድሞ የህወሓት አባላት አቶ ገብሩ አስራትና አቶ ሰዬ አብርሃ፤ እንዲሁም ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳና ሌሎችም ደጋግመው የተናገሩት በሥልጣን ዘመናቸው ከፈጸሟቸው እንደዋና ስህተት የሚያዩት በኤርትራ ጉዳይ ላይ የወሰዱት አቋም መሆኑን ነው። ሀገሪቱንም ሙሉ በሙሉ የባህር በር ማሳጣትን ጭምር እንደሆነ ይናገራሉ። ነገር ግን ህወሓት/ኢህአዴግ አሁንም ይህን ስህተቱን ለማረም ሳይሆን በከፋ መልኩ ሀገሪቷን የሚጎዳ ነገሮችን ይፈጽማል። የህወሓት/ኢህአዴግ ዋና ተቀዳሚ ተግባር አምባገነኑን ሥርዓት በሥልጣን ማቆየትና ማስቀጠል ብቻ ነው። ይህንንም ለማድረግ

የማይፈነቅለው ድንጋይ የማይበጥሰውት ቅጠል አይኖርም። ይሁን እንጂ የህወሓት/ኢ.ህአዴግ ሥርዓት ከመበስበሱ የተነሳ ሊጠገን ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። የሥርዓቱ ውስጣዊ ቅራኔ ከመባባሱም በላይ እከሌ ከከሌ ሳይባል ከቀበሌ ሹማምንት ጀምሮ እስከ ጦር ጄነራሎቹ ድረስ ያሉ ባለሥልጣናት በሙሰኝነት ከመዘፈቃቸውም በላይ ሙሰኝነት በሥርዓቱ ውስጥ ሥር በመስደዱ መቀልበስ ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። አገዛዙ ዓይን ባወጣ ዝርፊያና በዘር አድልዎ ከመጨመላለቁ ባሻገር የኑሮ ውድነቱ፣ ሥራ-አጥነቱ፣ ግፍና ሰቆቃው ሞልቶ ተትረፍርፏል። በዚህም የተማረሩት የሀገሪቱ ዜጎች በገፍ በየአቅጣጫው ሀገር ጥለው በመሰደድ ላይ ናቸው። ሀገሪቷን ሊታደጋት የሚችለው ምሁር በአስፈሪ መልክ አገር ጥሎ እየተሰደደ ነው። የሥርዓቱ ባለሥልጣናት በሥርዓቱ ቀጣይነትን እምነት በማጣታቸው የተነሳ የሀገርን ንብረትና ገንዘብ ወደ ውጭ አገር እያሸሹ ነው። ሥርዓቱ በአጠቃላይ የዜጎች የኑሮ ዋስትናና ደህንነት መጠበቅ ተስኖታል። ከግብፅም ሆነ ከሱዳን፣ ከሻዕቢያም ሆነ ከአልሸባብ ጋር የሚደረግ ስምምነትም ሆነ መፋቀር የሀገሪቷን ምስቅልቅል ሁኔታ ሊፈታው አልቻለም፣ አይችልምም። የሀገሪቷን ችግር ሊፈታው የሚችለው አማራጭ አንድና አንድ ብቻ ነው፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚደረግ ስምምነት!

የአሜሪካ የስለላ ድርጅት የመረጃ መዝገብ (C.I.A Fact Book) እንደሚያሳየው በ2013 የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 93 ሚሊየን ደርሷል። ከዚህ የሕዝባችን ቁጥር ውስጥ 25-54 ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት 29.1% ብቻ ሲሆን 64.3% የሚሆነው ደግሞ ከ24 ዓመት ዕድሜ ክልል በታች ነው። ይህ ወጣት ትውልድ ትምህርት፣ የጤና አገልግሎትና ሥራ ይፈልጋል። የጥቂቶች መጠቀሚያ የሆነው ሥርዓት አብዛኛውን ሕዝብ የበይ ተመልካች ያደረገው ሥርዓት በወጣቱ ዘንድ ጨርሶ ተቀባይነት የለውም። ይህንን ዘረኛነት፣ አድሏዊነት፣ ግፍና ሰቆቃ የተሞላበት ሥርዓት ወጣቱ ጨርሶ ሊሸከመው አይችልም። ይህ ሁኔታ በአስቸኳይ ተለውጦ ሁሉም በሀገሩ እኩል ተጠቃሚ መሆን ካልተቻለ ከአርባ ዓመት በፊት በየካቲት 66 በድንገት የፈነዳውን ዓይነት ሕዝባዊ ማዕበልና አመፅ በድጋሚ መፈንዳቱ እንደማይቀር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። የአፋኝ ሥርዓት መጨረሻው በሕዝባዊ ማዕበል ተጠራርጎ መውደቅ መሆኑን የዓለማችን ክስተቶችም አረጋግጠውታል። ከሃምሳ እስከ ሰባ ዕድሜ ያስቆጠሩት የምሥራቁ የሶሻሊስት ካምፕ አምንባገነን ሥርዓቶች በሰማኒያዎቹ መጨረሻ ላይ በሕዝባዊ ማዕበል መናድ የሚጠቁመውም ይሄንኑ ሃቅ ነው። አሁንም በቅርቡ "የዓረብ ስፕሪንግ" ተብሎ የሚታወቀው ሕዝባዊ ማዕበል ከሠላሳ እስከ አርባ ዓመታት የቆዩ አንዳንድ የዓረቡ ዓለም አፋኝ አገዛዞችን ገፍትሮ መጣሉ ሌላው ማረጋገጫ ነው።

ስለዚህ የአንድነት ኃይላት የሀገራችንንና የዓለምአቀፋዊ ሁኔታ በጽሞና በመመርመር አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገን ካልተንቀሳቀስን አሁንም በድጋሚ ለሌላ ዙር አምባገነንና ላልታሰበ እልቂትና አለመረጋጋት መጋለጣችን አይቀሬ ነው። ይህ በሀገራችን ላይ የተደቀነው ሥጋት እንዲወገድና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመሥረት የሚደረገው ትግል እንዲሳካ ከተፈለገ በቀጠናው ውስጥ ያሉትን ኃይሎች የመጨረሻው ዓላማና ግባቸውን በመገንዘብ አጋርና ጠላታችንን መለየት ይኖርብናል። እንዲሁም ሕዝባችንን አሰባስበንና

ኃይላችንን አቀናጅተን ትግሉ የሚጠይቀውን ሕዝባዊ የአንድነት ኃይል መፍጠር ተቀዳሚ ተግባራችን መሆን ይኖርበታል እንላለን።

በዜጎቻችን ላይ የሚደርሰው ግፍና ሰቆቃ ያክትም!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!